ዲ. ሰሎሞን ዮሐንስ
69

ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
D.N Solomon Yohannes
0911860113
0111/271609

# ፍኖተ ጥበብ


ከአስረስ የኔሰው

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ዘኢትዮጵያ ፡ በሠላሳ ፡ ስድስተኛው ፡ ዓመተ ፡ መንግሥት ፡
፲፱፻፶፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ታተመ ።

አዲስ አበባ ፲፱፻፶፰ ዓመተ ምሕረት

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ ።

www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ።
ዘውእቱ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ።

Solomon Yohannes 0911226073 0114227609

www.ethiopianorthodox.org

መግለጫ ።

የኖኅ ፡ መንግሥት ፡ ለ፫ት ፡ ሲከፈል ፡ በካም ፡ ቤትም ፡ የወረደው ፡ መንግሥት ፡ ለ፫ት ፡ ሲከፈል ።

በኩሳ ፡ በኩል ፡ የወረደው ፡ ከቋንቋ ፡ መረገም ፡ አስ ቀድሞ ፡ ካም ፡ ወደ ፡ አፍሪካ ፡ አምጥቶት ፡ በኩሳ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የነበረው ፡ ግዕዝ ፡ ፊደል ፡ በኩሳ ፡ ቤተ ፡

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፳፫ኛ | ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ | |
| ፳፬ኛ | ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ | |
| ፳፭ኛ | ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ | |
| ፳፮ኛ | ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| በኋላ፡ የተጨ | ኰ | ኲ | ኵ | ኳ | ኴ |
| መሩ፡ ናቸው፤ | ቈ | ቊ | ቍ | ቋ | ቌ |
| የግዕዝ ፡ ዲቃ | ጐ | ጒ | ጕ | ጓ | ጔ |
| ሎች ፤ | ዀ | ዂ | ዅ | ዃ | ዄ |

ለሚአስተውል ፡ የጥንታውያኑ ፡ ፊደሎች፡ ቍጥርና ፡ ይህ ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ።

ለመረዳት ፡ ፊላጊ ፡ ቢኖር ፡ ቍጥሩና ፡ ፊደሎች ፡ ትክክል ፡ አለመሆናቸውን ፡ ያስተውል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፍኖተ ፡ ጥበብ ፡ የጥበብ ፡ ጐዳና ።

### ቀዳሚሃ ፡ ለጥበብ ፡ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ።

አስቀድሞ ፡ ለሰዎች ፡ ልጆች ፡ መማር ፡ የሚገባው ፡ ፩ኛ ፤ የፊደሎችን ፡ መልክ ፡ ነው ። ፪ኛም ፡ ሰባቱን ፡ ዕለታት ፡ ነው ።

የፊደሎቹ ፡ መልክና ፡ ቁጥር ።

ዋናው ፡ መሠረት ፡ ቁጥር ፡ ነው ። ቁጥሩም ፡ ፊደል ፡ ነው ።

ሥላሴ ፡ ዓለምን ፡ ሲፈጥሩ ፡ በቁጥር ፡ ነው ። ያለ ፡ ቁጥር ፡ የተሠራ ፡ ነገር ፡ የለም ።

አሁን ፡ የምንፈልገው ፡ ለሕፃናቱ ፡ የሚሆነውን ፡ የፊደሎችን ፡ መልክና ፡ ቁጥር ፡ እንዲአውቁ ፡ ነው ።

### ፪ኛ ፤

የፊደሎችን ፡ መልክ ፡ ካወቁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ማጋገዝና ፡ ማንበብ ፡ ይራመዳሉ ። ይህም ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ሀ ፡ ግዕዝ ፤ ሁ ፡ ካዕብ ፤ ሂ ፡ ሣልስ ፤ ሃ ፡ ራብዕ ፤ ሄ ኃምስ ፤ ህ ፡ ሣድስ ፤ ሆ ፡ ሳብዕ ፤ እንደዚህ ፡ እያሉ ፡ ፳፯ቱን ፡ የግዕዙን ፡ ፊደላት ፡ ይጨርሳሉ ፡ ማለት ፡ ያጠናሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

ሥራቅ ፡ ያለው ፡ ሲደመር ፡ ፊክ ፡ ፫፻፷፭ት ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ኢ/ ቤተ ፡ ክ/ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ መሠረት ፡ ይገኝባታል ።

የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ ይህንን ፡ መሠረት ፡ ባለማወቅ ፡ ፊደሎችን ፡ እንቀንስ ፡ ሲሉ ፡ ይገኛሉ ። ስለዚህ ፡ ይህች ፡ ማስታወሻ ፡ ባ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. በመስከረም ፡ ወር ፡ ተጻፈች ።

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org